**የኢህአዴግ የምርጫ ምልክት**

**የኢህአዴግ የአዲስ አበባ ፅ/ቤት** **የምርጫ ቅስቀሳ ፅሁፍ፣ ቁጥር 1 የካቲት**

# የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች!

**በከተማችን ለሶስተኛ ጊዜ በሚካሄደው የአካባቢ አስተዳደርና ከተማ አቀፍ ምርጫ ኢህአዴግ እንደተለመደው የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ፍላጐታችሁን ለማሟላት በተወዳዳሪነት ቀርቧል። ምርጫው ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች እድገትና ተጠቃሚነት ወሳኝ የሆኑት የቀበሌ፣ የክፍለ ከተማና የከተማ አስተዳደር አካላት የሚቋቋሙበት በመሆኑ ኢህአዴግ በተሳታፊነት ሲቀርብ ከተማዋን የማስተዳደር ሃላፊነቱን ብትሰጡት ከመቼውም ጊዜ በተሻለ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማታችሁን፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጥማታችሁን ለማርካት ፍላጐቱ ብቻ ሳይሆን ዝግጁነቱ እንዳለው በመተማመን ነው። ኢህአዴግ በአጠቃላይ አገራችንን በእድገትና ህዝብ ተጠቃሚ በሚሆንበት ጐዳና ለመምራት በተለይ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የከተሞችን እድገት ለማፋጠን ባደረገው ርብርብ ያካበተውን የመምራት ችሎታና ልምድ ለናንተ የላቀ እድገትና ተጠቃሚነት ሊያውለው ተዘጋጅቷል።**

## ለአዲስ አበባ ልማት መፋጠን፣ ለመልካም አስተዳደር መስፈንና ለነዋሪዎች ተጠቃሚነት ኢህአዴግን እንምረጥ!

በሶስተኛው የአካባቢና የከተማ አስተዳደር ምርጫ ላይ ሁለት በአላማቸውና በአሰራራቸው የተለያዩ ሃይሎች እናንተ ፊት ለመወዳደር ቀርበዋል። በአንድ በኩል ከተሞችን ጨምሮ መላ አገራችንን በፈጣንና ከፍተኛ የእድገት ምጣኔ አቅጣጫ ማስጓዝ የሚችል አስተሳሰብና የመፈፀም ችሎታ ያለው ኢህአዴግ ተሰልፏል። በሌላ በኩል ደግሞ ለልማታችሁና ለመልካም አስተዳደር ፍላጐታችሁ እውን መሆን በማይበጁና በተውገረገሩ ሃሳቦች የሚመሩት፣ ከሰጣችኋቸው ሃላፊነት ታማኝ መሆን አቅቷቸው መሃል ሜዳ ላይ ትተዋችሁ የሄዱት ተቃዋሚዎች ተሰልፈዋል። በነዚህ ሁለት ሃይሎች መካከል ያሉት ልዩነቶች በተለይ ባለፉት ጥቂት አመታት ከመቼውም ጊዜ በላይ በማያሻማ ደረጃ ትክክለኛውንና የተሳሳተውን፣

ጠቃሚውንና ጐጂውን በንድፈሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባር ለመለየት በሚያስችል አኳኋን ታይተዋል::

ለሁላችንም ግልፅ እንደሚሆነው ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይና በፊት የሚያሳስበው ጉዳይ የአገራችን እድገትና የዜጐችና የህዝቦቿ እኩል ተጠቃሚነት ነው:: ከዚህ በመነሳት በከተማም በገጠርም ልማትን የሞት የሽረት ጉዳይ አድርጐ እየተረባረበ ይገኛል:: ይህ ርብርብ በግምትና በቅን ፍላጐት ብቻ የሚመራ ሳይሆን መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል የልማትና የዴሞክራሲ አላማና ስትራቴጂ እየተመራ ተግባራዊ በመሆን ላይ የሚገኝም ነው:: በዚህ መሰረት ኢህአዴግ አብዛኛው የአገራችን ህዝብና የልማት አቅም በሚገኝበት ገጠርና ለገጠሩና ለራሱ ለከተማው እድገት ቁልፍ ሚና ባላቸው ከተሞቻችን በሙሉ የተፋጠነ ልማት ለማምጣት ተረባርቧል:: በመጀመሪያዎቹ አስር አመታት በየአመቱ በአማካይ 6 በመቶ እድገት ሲያስመዘግብ የቆየው ኢህአዴግ በመጨረሻዎቹ አምስት አመታት አማካይ አመታዊ የኢኮኖሚ እድገታችን ከ11% በላይ አድርጐታል:: ይህ አመታዊ እድገት ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ አሃዝ መደርደር ይወዳል በሚሉት ስሌት ሳይሆን በተጨባጭ የተከናወኑ የልማትና እድገት ተግባራትና ውጤቶች መልክ የሚገለፅ ነው::

በአገራችን ገጠሮች በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ያለውን የምርታማነት፣ የኮመርሻል ግብርናና የልዩ ልዩ ማህበራዊ እድገቶች ለጊዜው ወደጐን አቆይተን በከተሞች ያለውን ሁኔታ ለሚመለከት በርግጥም አገራችን በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም::

ዛሬ መላውን የአገራችንን ከተሞች ጨምሮ በተለይ በአዲስ አበባ እጅግ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትና ግስጋሴ እየታየ ነው:: የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለግምት በሚያስቸግር ፍጥነት እያደገ ነው:: ከተማችን በየቀኑ እየተቆፈረች ህንፃዎች ቅፅበታዊ በሆነ ፍጥነት እየተገነቡ በአምስት አመት በቀላሉ የማትታወቅበት ለውጥ አምጥታለች:: ለውጡ ለመኖሪያና ሌላ አስፈላጊ የሆኑ ህንፃዎችን በመገንባት ሳይወሰን ሰፊ የኢንዱስትሪ ተቋማትን በመገንባትም ጭምር እውን ሆኗል:: የግሉ ሴክተር ከሚያካሂደው ግንባታ ባልተናነሰ በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የነዋሪዎቿ መሰረታዊ ችግር ከሆኑት አንዱ የሆነውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል በሁለት አመት ብቻ 31ሺ ያህል የጋራ የመኖሪያ ህንፃዎች ገንብቶ ለተጠቃሚዎች አስተላልፏል:: ይኸው የቤት ልማት ፕሮግራም አሁንም በመቀጠል ላይ ይገኛል::

የከተማዋን መንገዶች በማስፋትና በማስፋፊያ አካባቢዎች አዳዲስና ሰፋፊ መንገዶችን በመገንባት ከተማችን ኢንቨስትመንት የመሳብ ተወዳዳሪነቷ ከፍ እንዲል ለነዋሪዎቿም በእጅጉ የተመቸች እንድትሆን ተረባርቧል:: የከተማውን ህዝብ የውሃ ችግር ለማቃለል፣ የኤሌክትሪክና የቴሌፎን አገልግሎት ተጠቃሚነት ለማስፋትም ያልተቆጠበ ጥረት አካሂዷል:: ኢህአዴግ

ልማታችን በጀማሪ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ሁሉንም የህዝብ ችግሮች ለመፍታት ጊዜው ገና እንደሆነ ቢገነዘብም ከተማችን በመሰረታዊ የለውጥ ጉዞ ላይ እንድትገኝ ለማድረግ የሚያቅተው እንዳልሆነ በማመን ባካሄደው ርብርብ ከመቼውም ጊዜ እየተሻሻለ የሄደ የህዝብ ተጠቃሚነት አረጋግጧል።


## የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች!

ኢህአዴግ የልማት የመጨረሻ ግብ ህንጻና መንገድ መገንባት ሳይሆን የዜጐች ገቢ ጨምሮ የኑሮ ደረጃቸው ተሻሽሎ መገኘቱን ማረጋገጥ እንደሆነ በጥብቅ ያምናል። በዚህ መሰረት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውና በግሉ ሴክተር በሚገነቡ ትልልቅ የምርትና የአገልግሎት ተቋማት ሰፊ የስራ እድል እንዲፈጠር ሁኔታውን ከማመቻቸቱም በላይ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ፕሮግራም ቀርፆ የከተማዋን ነዋሪዎች የስራ እድልና ገቢ ለማስፋት ተረባርቧል። በአጠቃላይ በአገራችን ታሪክ በተለይ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የክፍለ ዘመን ጉዞ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት በአጭር ጊዜ ሴክተሩን ለመገንባት ተረባርቧል። ከምርጫ 97 በፊት ከተማዋን በሃላፊነት ባስተዳደረባቸው የመጨረሻ አመታት ወጣቶችና ሴቶችን አደራጅቶ፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎችን አመቻችቶና ህንፃዎችን ገንብቶ የብድር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ እየሰጠ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ልማት በሰፊው እንዲሳተፉ ማድረግ ጀምሮ ነበር። በዚህ ጥረቱ ብዙዎች የስራ እድል ከማግኘት አልፈው አስተማማኝና እያደገ የሚሄድ የገቢ ምንጭ ማግኘትም ጀምረው ነበር። ዛሬም በዚሁ አቅጣጫ ተጉዘው ተጠቃሚነታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ያረጋገጡ ወጣቶችና ሴቶች ቁጥር ጥቂት አይደለም። ይህ ሂደት በምርጫ 97 ሃላፊነቱ የተሰጣቸው ተቃዋሚዎች በፈጠሩት ትርምስ ባይቀጭ ኑሮ ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችል እንደነበር ሳይታለም የተፈታ ነው።

በማህበራዊ ልማት መስክም በአዲስ አበባ ከተማ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት በማሰብ ኢህአዴግ በከፍተኛ ደረጃ ተረባርቧል። ህዝቡን አስተባብሮና በመንግስት አቅም ባካሄደው ግንባታ በሁለት አመት ውስጥ ብቻ 250ሺ ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችሉ 100 የትምህርት ቤት ህንፃዎችን ገንብቶ የፈረቃ ትምህርትን አስቀርቷል። በጤናውም መስክ የተለያዩ የጤና ተቋማትን በመገንባት ህዝብ የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል። ምንም እንኳ በነዚህ ሁሉ መስኮች የመጡት ለውጦች ጅምር በመሆናቸው መላውን ነዋሪ በሚጠቅምና በሚያረካ ደረጃ የተፈፀሙ እንዳልሆኑ ኢህአዴግ የሚገነዘብ ቢሆንም በትክክለኛው የለውጥ ጐዳና መራመድ ከመጀመር አልፈው በአጭር ጊዜ ሰፊና ስርነቀል ለውጥ ማምጣት እንደጀመርን ግን ይተማመናል።

ኢህአዴግ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ የሚቻለው እድገትን በማፋጠን ነው ብሎ በማመን ሌት ተቀን በልማት ላይ ሲረባረብ ተቃዋሚዎች ግን የተሰራውን በማብጠልጠል ስራ ላይ ብቻ ተሰማርተው እንደቆዩ ይታወቃል፡፡ ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው እንዲሉ በልማቱ ተግባር ላይ ለመደጋገፍ ፍላጐቱም ብቃቱም የሌላቸው ተቃዋሚዎች ባለፉት አመታት እንደተመለከትነው ዋነኛ ስራቸው የተሰራውን ማብጠልጠል ነበር፡፡ «ኢህአዴግ ለገጠሩ ብቻ ነው ትኩረት የሚሰጠው ከተማውን ግን ረስቶታል» በሚል መሰረተ ቢል ቅስቀሳ በከተሞች የልማት እንቅስቃሴና ውጤት የሌለ ለማስመሰል ተረባርበዋል፡፡ መንግስት የዜጐችን የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል አሮጌ ቤቶችን አፍርሶ፣ ለዜጐች ተገቢውን ካሳ ከፍሎ መሬትን ለተስፋፋ ልማት ሊያውል ሲረባረብ በዚህ ሂደት የተፈጠሩ ጊዜያዊ ስሜቶችንና ጉዳቶችን አጋኖ በማቅረብ ህዝብ በራሱ ልማት ላይ እንዲያምፅ ሲያስተምሩ ከርመዋል፡፡

በመጨረሻም የከተማችን ነዋሪዎች በምርጫ 97 የሰጧቸውን ከተማ የማስተዳደር ስልጣን ፈፅሞ ሃላፊነት በጐደለው አኳኋን አንረከብም ብለው ህዝቡን ሜዳ ላይ ጥለውት ቀርተዋል፡፡ ዛሬ በከተማችን ህዝብ ፊት ለውድድር የቀረቡት ተፎካካሪዎች እነዚህ ናቸው፡፡ ለልማታችሁ መፋጠንና ለተጠቃሚነታችሁ ሳይታክት የሚሰራው ኢህአዴግ በአንድ በኩል፣ ታላቋን መዲናችንንና ሀብትዋን የማስተዳደር ብቃት የሌላቸው ብቻ ሳይሆን ካለፈው ተግባራቸው በመነሳት አመኔታ የማይጣልባቸው ተቃዋሚዎች በሌላ በኩል በተወዳዳሪነት ቀርበዋል፡፡ ፈጣን እድገትን በማምጣት ለተጠቃሚነታችሁ በር የከፈተውንና ይህንንም የማስፋት ብቃት፣ ፖለቲካዊ ዝግጁነትና ድርጅታዊ ጥንካሬ ያለውን ኢህአዴግን በመምረጥ ተጠቃሚነታችሁን አብረን እናረጋግጥ ዘንድ ኢህአዴግ ጥሪውን ያቀርብላችኋል፡፡



**የምርጫ ምልክታችን ችቦ ነው፡፡**